# አስራትን ስንዘክር

አገሬ ከስዊድን
2012-05-12

ኢትዮጵያ ቀን ጥሏት ፤ በባንዶች እጅ ወድቃ
ህዝቡ በሰመመን ፤ ሲያሸልብ ሳይነቃ
አንድ የቁርጥ ቀን ፤ ልጅ አስራትን አግኝታ
ላመነበት ነገር ፤ የማያመነታ
የሀገር መድህኒት ፤ የወገን አለኝታ
በባንዶች ቅንብር ፤ ተጠቃ ተመታ ።

ባንዳው የባንዳው ልጅ ፤ ጨብጦ ስልጣን
ኢትዮጵያን ሲያደማ ፤ ሲያጠፋ አማራን
አንድነት ሲናጋ ፤ በዘር ሲለየን
ብቸኛ ጠበቃ ፤ አስራት ነበረን ።

አስራት ምን ባጠፋ ፤ መከራ ተጋተ
ጀግንነት ስላለው ፤ በአያቱ የባተ
ከአገር በፊት ወጥቶ ፤ ስለተሟገተ
ግዞት ጥሪው ሆኖ ፤ በመለስ ታገተ ።

አስራት ምን ባጠፋ ፤ ለሞት ተዳረገ
የክብር ሞት መሞት ፤ ባህል ስላረገ
አገሩን ወገኑን ፤ በነፍሱ ታደገ ።

ፕሮፌሰር አስራት ፤ የአገር መድህኒት
ስንቱን በጥበቡ ፤ ቀዶ ፈውሶት
እንደ ውድ አባቱ ፤ እንደ ሰማዕት
እሱም በባንዶች ግፍ ፤ አልፏል በፅናት ።

ከአባቱ ከአያቱ ፤ ኖሮት ማስተዋል
በዋልጌዎች ጥፋት ፤ በባንዶች ተንኮል
አልገዛም ብሎ ፤ አሻፈረኝ ቢል
ዳኝነት ቢጠፋ ፤ ፍርድ ቢጓደል
አስራት ለሀገሩ ፤ መስዋዕት ሆኗል ።

አስራትን አድናቂ ፤ አወዳሽ አክባሪ
ባለ አደራው ትውልድ ፤ አስራትን ዘካሪ
ለአንድነት አሳቢ ፤ ለአገር ተቆርቋሪ
ፈለግ አስራት ይሁን ፤ የእያንዳንዱ ጥሪ ።

አስራትን ስንዘክር ፤ ሰንጠራ ስሙን
ቃል መግባት አለብን ፤ ልንይዝ አርማውን ።

የአስራትን ስንዘክር ፤ ተሰልፈን በአንድ
ቆርጠን እንነሳ ፤ ሳንንገዳገድ
የአስራትን ፈለግ ፤ ይዘን ለመንጎድ ።

አስራት ለድንበሩ ፤ አስራት ለአንድነቱ
አስራት አስተዋዩ ፤ ለሰብአዊነቱ

EthioLion.com

በማተቡ ፀንቶ ፤ እንቢ በማለቱ
ከፍሏልና ነፍሱን ፤ እንደ አባት አያቱ ።

እኛም የሱ ልጆች ፤ በእሱ የምንኮራ
የውሻ ሞት ሲሞት ፤ በኢትዮጵያ አማራ
ባይተዋር አንሁን ፤ ጠላት ሲያንሰራራ
ቆርጠን እንቀበል ፤ የአስራትን አደራ ።

መሞትም ካለብ ፤ እንሙት በኩራት
ለሀገር ለወገን ፤ በመቆም በፅናት ።

EthioLion.Com